# የዘረኝነት ኣደጋ በኢትዮጵያ

ኣንዳንድ ግዜ ይህቺ ያልታደለች ኣገር ያሰኛል። ከኣፄ ኃይለስላሴ ግዜ ጀምረን እስከ ደርግ ፍፃሜ ስንሰቃይ ብሎም ማንነታችን ጭራሹ ሊጠፋ ተቃርቦ ነበር። ህዝባችን በራሃብ ኣለንጋ ሲገረፍ የሚወዳትን ኣገሩ ለቆ ሲሰደድ የኣለም ሕዝብ መነጋገርያ ሆኖ ነበር። ንፁህ ዜጋ ያደረገው ነገር ሳይኖር በኣደባባይ ሲረሸን መውጫ የሌለው ወደ ሚመስለው ችግር ገብተን ነበር። ችግሩ ሌላ መፍትሄ የሌለው መሆኑ የተረዱ ጀግና የህዝብ ልጆች በማንኛውም ማስፈራራትና ጉራ ሳይበገሩ ራብን ጠማን ሳይሉ ለረጅም ግዜ ቆራጥ ትግል በማድረግ ውድ ህይወታቸውን በመሰዋት እስከ ኣፍንጫው የታጠቀ የደርግ ሰራዊት በማሸነፍ ህዝቡን ነፃ በማውጣት በ1983 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኣዲስ ምእራፍ ጀመሩ። ከዛም ኣልፈው የኣሸናፊነት ስሜት ሳይሰማቸው በኣገሪቱ ኣለ የተባለውን ብሄር፣ብሄረሰብ እና ህዝብ በማሳተፍ ኣዲስቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ደፋቀና ሲሉ በጦርነቱ የተሸነፉ ሆኖም ሽንፈቱ ያልተዋጠላቸው የኢሰፓ ይሁኑ የኢህኣፓ ኣባላት ግን የሚገነባውን ሲያፈርሱ እንቅልፍ ኣጥተው ቆይተዋል። ይሁንና ኣካሄዳቸውና ስልታቸው ግን እንደዛሬ እረቃኑ ኣልወጣም ነበር።

ከለውጥ በኋላ ባንጻሩ ህዝብ ተመኝቶት የነበረ ግን ጠንካራ የሆነ ሁሉም-ኣቀፍ አማራጭ ሊሆነን የሚችል ፓርቲ ይፈጠራል የሚል ነበር። ይህ ፓርቲ ዘር፣ቋንቋ፣ኃይማኖት ይሁን ሌላ መለያ መሰረት ሳያደረግ ከሁሉም ህብረተሰብ የሚፈጠር በሎም ለሁሉም ህብረተሰብ ጥቅም የሚቆም መሆን እንዳለበት ኣያጠራጥርም። በኣንጻሩ ግን የተፈጠሩት ፓርቲዎች ለኣንድ ብሄር የቆሙ ብቀላና ትላቻ መሰረት ያደረጉና ኣንድ ህዝብ እንደጠላት የፈረጁ ናቸው ሆኖው የተገኙት። እነዚህ ኣማራጭ ነን የሚሉ ፓርቲዎች የመጨረሻ ጠላት ኣድርገው የቆጠሩት የትግራይ ህዝብ ነው። ይሄን ህዝብ ለማጥፋት ኣመቺ ግዜና ሁኔታ ብቻ ነበር የሚጠባበቁት። እድላቸው ሆኖ ግን ኣመቺ ያሉት ግዜና ሁኔታ በኣንፃሩ ሆኖ ይገኛል። በነሱ ኣስተሳሰብ ባለፈው ምርጫን በማስታከክ የተጠቀሙትን ተጠቅመው የናፈቃቸውን ስልጣን ኮርቻ ላይ መፈናጠጥ የመጨረሻ እድላቸውን የሚተገቡሩበት አጋጠሚ ቀላል መስሎ ነበር የታያቸው። ለዚህም ይጠቅመናል ያሉትን መርዝ ሁሉ ያለምንም ገደብ በትግራይ ህዝብ ላይ ሲረጩ ተሰተውለዋል። በኣባታቸው ደርግ ጊዜ የተባሉትን ሁሉ በመተው እነሱ ራሳቸው በምርጫው ዋዜማ ያሉትን ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ፣

- ትግሬ ወደ መቀሌ ንብረት ወደ ቀበሌ (በኣዲስ ኣበባ ሰልፈኞች የተደምጠው መፈክር)
- ወደ መጡበት እንመልሳቸዋለን (የፓርቲ መሪዎች በተለያዩ ግዜ የገለጹት)
- "ለትግሬ ችጋር ብዬ ነው ደጅ የጠናሁት እንጂ ደጅ ጠንቼ ኣላውቅም" (ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርም በምርጫ ክርክር ከተናገሩት)
- ከተማ ሊያስተዳድሩ ቀርቶ የከተማ ንሮ በማያወቁ ነው ከተሞች የሚተዳደሩት (ከአዲስ ኣባባ ከተማ ኣስተዳደር በተያያዘ ኣቶ ልደቱ ኣያሌው በምርጫው ክርክር ከተናገሩት)
- ለመናገራቸው ለህሊና የሚሰቀጥጥ ቋጠሮ በተባለ የኢንተርኔት መርበብ (በግጥም መልክ) ህዝብን በሚዘልፍ መልኩ የሚነገሩና የሚጻፉ
- ሌላም ሌላም

በኣጭሩ በኣሁኑ ግዜ ኣይነ ያፈጠጠ የዘረኝነት መርዝ በመርጨት ላይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች በፍፁም የማይወክሉ፣ ብሎም ባለፉት ኣምባገነናዊ መንግስታት በኣመራር ደረጃ ይሁን በቢዝነስ የተንደላቀቀ ንሮ ይኖሩ የነበሩና ሥር-የሰደደ የብቀላ ኣላማ ያላቸው ቡዱኖች ናቸው::
በኢትዮጵያ ያለውን ልዩነት በጭራሽ የማይወክሉ መሆናቸውንና ትክክለኛ ባህርቸውን እንዳይታወቅባቸው ለመሸፋፈን የሚጠቀሙበት የቅትፈታቸው ዘዴ ደግሞ ያው የተለመደው ከነሱ በላይ ለኢትዮጵያ ኣሳቢ እንደሌለ የኣዞ ዕንባ በማንባት የውሸት ኢትዮጵያ ኣገሬ ኣይነቱ ቀረርቶ መዝፈን ነው:: ለምሳሌ ያህል ሌላው ግዜ ያለፈበት ዘዴ ደግሞ ለይስሙላ በሕወሓትና በትግራይ ህዝብ የተጠሉ በትግል ሜዳ ሊጠብቁት የተሰጣቸውን ደፈጣ ለጠላት ኣሳልፈው የትግራይ ሕዝብ በፈታኝ ግዜው ጥለውት ወደ እሚመቻቸው የፈረጠጡ ግለሰቦችን በማግባባትና በማሰለፍ ፓርቲያቸው ህብረ-ብሄራዊና ሁሉም ኣቀፍ ለማስመሰል ሞክረዋል:: የነዚህ ግለሰቦች ታሪክ ሲታይ ደግሞ ለህዝብ ቀርቶ ለራሳቸው እንኳን የማይሆኑ ናቸው:: ኣንድ የሚያደርጋቸው ዓላማ ቢኖር ኢህኣዴግን መጥላታቸው ብቻ ነው::

ሌላው ቀርቶ በውጭ የሚገኙ የነኚህ ፓርቲዎች ደገፊዎች በየኢምባሲውና በተባበሩት መንግስታት ጽሕፈት ቤቶችን የሓዘን ልብስ ለብሰው በመሄድ የውሸት የሚያለቅሱትን ግለሰቦች ምንነት ሲታይ ከላይ የተጠቀሰውን ሃቅ የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል:: ማንም ሰው ማረጋገጥ እንደሚችለው በውጭው ኣለም በኣሁኑ ሰኣት በመንጫጫት የሚገኙት ግለሰቦች መላው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የማይወክሉ ያለፈውን ኣገዛዝ ለመመለስ ከንቱ የሚፍጨረጨሩ ብቻ ናቸው:: እነዚህ ግለሰቦች ኢትዮጵያ ሊወክሉ ይቅርና የራሳቸው ብሔርም በጥቂቱ አንኳዋን ኣይወክሉም:: የሚናገሩትም ክስ ካለነሱና ጥቂት ደጋፊዎቻቸው በሰተቀር ማንንም ኣይወክልም:: የሚያሳዝነው ደግሞ የኣሜሪካ ድምጽ ሬድዮና ዶቸ ቬለ እንደ ድሮኣቸው በኢትዮጵያ ስም ግልፅ በሆነ መልኩ ወገናዊነታቸው ለነዚህ ዘረኞች ብቻ ማሳየታቸው ነው:: ለመላው የኣገሪቱ ህዝብ ጠቃሚ ለሆኑ ነገሮች ሊውሉ የሚገባቸው ሬድዮ ጣብያዎች በአሉባሌ ነገር ማዋላቸው (ሚስዩዝ ማድረጋቸው) እጅጉን በጣም ያሳዝናል::

እነዚህ በኣሁኑ ሰኣት በዪኢምባሲዎቹ ጽህፈት ቤት "ሃዘናቸውንና " እሮሮኣቸውን በመግለጽ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በጣም ዘረኞች መሆናቸውን ለመግለጽ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፤ ይኸውም በትክክል ለኢትጵያ ህዝብ ያለ ኣድልኦ የሚቆረቆሩና የሚያዝኑ ቢሆኑ ኖሮ ምነው በ1990 ዓ.ም. መቀሌ ውስጥ ምንም የማያውቁ ህጻናት እየተማሩ በነበሩበት ክፍል ውስጥ በግፍ ሲታረዱ ለምን እንደ ኣሁኑ ጥቁር ልብስ በመልበስና በዪኢምባሲዎቹ በመሄድ ሃዘናቸውንና እሮሮኣቸውን ኣልገለጹም? በቁጥርም ቢሆን በዛን ጊዜ የሞቱ ህጻናት ይበልጡ ነበር::ታድያ ምነው ይኸ ግልጽ የሆነ ዘረኝነታቸው በኣደባባይ ማውጣታቸው? ታዲያ ለማን እንደቆሙስ የበለጠ ግልጽ እያደረጉት ኣይደለምን?

በማጠቃለል ለማለት የሚቻልው ይሄን ኣይነቱ ዘረኝነት ካልተተወ በስተቀር በኢትዮጵያ ሰላምና እድገት ለማምጣት እጅጉን በጣም ኣስቸጋሪ ነው የሚሆነው:: አብሮ መኖር እራሱ በኣደጋ ላይ ነው የሚወድቀው:: ቀጥሎም በኣጠቃላይ የኢትዮጵያ ህልውና በጥያቄ ምልክት ውስጥ ይገባል:: ይህ ማለት ደግም ማናችንም ተጠቃሚዎች ኣንሆንም:: ምናልባት ውጪ ያላችሁ ብቻ

ምንነታችሁን ተዋርዶ የልመና ምግብ እዬበላችሁ ትኖሩ ይሆናል:: ኣገር ውስጥ ያለው ህዝብ ግን ለበለጠ ድህነትና ውርደት ይጋለጣል:: እነሆ በቅረቡ ግዜ እንኳን በነዚህ 'እኔ ካልኖርኩበት ሰርዶ አይብቀልበት' ባይ ቡዱኖች ሰበብ በእንግሊዝ መንግስት ሊዘረዝ የነበረው በሚልዮን የሚቆጠር ዕዳ እንዲቆይ ተደርገዋል:: ይኸው ደግሞ ድኃው ህዝብ ነው የሚጎዳው::

በተጨማሪ ግልጽ መሆን የሚገባው ነገር ካለ ደግሞ የፈለገ ነገር ብታደርጉ የፈለጋችሁትን የዘረኝነት መርዛችሁን ብትረጩ ተመልሶ እናንተን ብቻ እንደሚፈጃችሁ ከወዲሁ ማወቅ ይኖርባችሁዋል:: ከታሪክና ካለፈው የመማር ኣቅማችሁ በጣም ደካማ ነው እንጂ የኣሁኑ ተግባራችሁ ቀደም ብሎ የተሞከረና ያልሰራ ኣካሄድ መሆኑን በተገነዘባችሁት ነበር:: ኣሁን የትግራይ ህዝብን እንደድሮው እናንበርክከዋለን ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ ማሰብ የሚችል ኣእምሮ የላችሁም እንጂ ሌላ ብታስቡበት ይሻላል::
ጨዋውና ጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በኣሁኑ ሰኣት የሚመኘውና የሚገባው ግን ችግሩን (ድህነቱን) የሚረዳለት፤የሚያከበረው፤እሱን መስሎ የሚኖር፤ከሌላ ጎረቤቶቹ ሰላምና ፍቅር የሚያመጣለትና በኣገሪቱ ለኣንዴና ለመጨረሻ ኣመጽና ብጥብጥ ስልጣንን ለመያዝ እነደ ኣማራጭ የማይወስድና የሚኮንን ህብረ-ብሄራዊ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚወክል ፓርቲ ነበር:: ይኸንን ለማዬት ግን ህዝቡ ኣልታደለም:: ይኸንን ኣማራጭ ትተው የድሮው ዘፈን የሚያምራቸውና ህዝብን ምዝለፍ የሚዳዱ ቡዱኖች ግን ከንቱ ልፋት መሆኑ እንዲገነዘቡት ይገባል:: በትግርኛ እነደተባለው እንኪንዶ ኣስናንኩም ሽሪፍኩምስ (ጎሪፍኩምስ) ምስ ኣስናንኩም እንክለኹም እኳ ኣይኮነልኩምን!! ወይም ደግሞ በደርጉ ገዜ "ግፍዕታት ደርግስ የሐርነናምበር ኣዬምበርክኸናን" እነዳልነው ሁሉ ኣሁንም መድገሙ የግድ ነው:: የናነተው ዘረኝነት የበለጠ እንድንነቃና ኣንድነታችንን እንድናጠናክር ያደርገናል እጂ አያንበረክከንም! እንግዲህ ልብ ያለው ልብ ይበል!
የእኩልነት፤የኣንድነት፤የሰላም፤የመከባበር፤ልዩነትን የመቀበልና፤የህግ በላይነት ሌላ ኣማራጭ የላቸውም:: ቢኖሯቸውም የማይፈለጉና ውጤት የሌላቸው ናቸው::